# ወቅታዊው የአገራችን ሁኔታ ያሳሰበንና በምእራብ አውስትራሊያ ነዋሪ የሆን ኢትዮጵያውያን መግለጫና ውሳኔ።




ዛሬ ሀገራችን የምትገኝበት አሳሳቢ ሁኔታ የሚያመለክተው ላለፉት 18 አምታት የኢትዮጵያን ህዝብ ቀጥቅጦ የገዛው ወያኔ የስልጣን ዘመኑ ፍጻሜ መቃረቡን በማወቁ፤ አጥፍቶ የመጥፋት፤ የደመ-ነፍስ እርምጃ እየወሰደ መሆኑን ነው ።

ወያኔ የሚያራምደው የተሳሳተና አድላዊ የኤኮኖሚ ፖሊሲ ያስከተለው ድህነትና የኑሮ መናጋት አስከፊነት አዲስ ክስተት ባይሆንም፤ በአሁኑ ወቅት በተለይ የኑሮ ውድነቱ ከመቸውም ጊዜ ተባብሶ ይገኛል።በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖረው ወገንም ለከፋ ድርቅና በሽታ እንዲጋለጥ ተደርጓል።

ይህ የወያኔ ቅጣት፤ የዓለም የገንዘብ ቀውስ ካስከተለው ጫናና፤ ይኸው ቀውስ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገናቸውን ለመርዳት ያላቸውን አቅም ከመቀነሱ ጋር ተዳምሮ፤ የብዙሀኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ እጅግ መራራና መሸከም ከሚቻለው በላይ አድርጎታል።

ይህ አስከፊ የኤኮኖሚና ማህበራዊ ሰቆቃ የህዝባዊ ቁጣና መነሳሳት ዋዜማ መሆኑን ጠንቅቆ የሚያውቀው ወያኔ ታዲያ ምላሹ እንደ አንድ አገራዊ ሃይል፤እንዳውም የመንግስትን ሃላፊነት እንደያዘ አካል፤ አገርንና ህዝብን የመታደግ ወይም ችግሩን ለመቅረፍ የመሞከር ተግባር ሳይሆን ልክ እንደባእድ ወራሪ የሃገሪቱን ውድቀት የሚያፋጥን ሌላ ዙር ዝርፊያና ሀብትን ማሸጋገር ነው የሆነው።

ዛሬ ወያኔው ልክ መሬትን ጠቅሎ በመያዝ ገበሬውን መፈናፈኛ አሳጥቶት እንደኖረው ሁሉ ከራሱ የኤኮኖሚ ሞኖፖሊና የንግድ ኩባንያዎች ውጭ የሚንቀሳቀሱ የሀገሪቱን ነጋዴዎችና ባለሀብቶች በተለያዩ ዘዴዎች በማጥፋት ብሄራዊ ኤኮኖሚውን ሙሉ በሙሉ የተቆጣጠረው ነው የሚመስለው።

የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና ተቋማትንም እንደግል ኩባንያው በመጠቀም የአባላቱና የደጋፊዎቹ መናኸሪያ አድርጓቸዋል። የከፍተኛ ትምህርት ተመራቂዎች የወያኔ አባልነት ቅጽ ካልሞሉ ሥራ የመያዝ እድል እንደሌላቸው የአደባባይ ሚስጥር ነው። በሀገር ኅልውናና ደህንነት ረገድ ያለውን ሁኔታ ስንመለከትም የወያኔ መንግስት ከሱዳን መንግስት ጋር በመመሳጠር ምእራባዊ የግዛታችንን መሬት ቆርጦ ለመስጠት የጀመረውን ጥረት እየገፋበት ይገኛል። ወያኔ የራሱን ጊዚያዊ ጥቅም እያስላ በጎረቤት አገሮች ላይ የሚፈጽማቸው ጣልቃ ገብነቶች ለሀገራችን ቋሚ ችግር እያወርሱ መሆኑንም የሱማሌ ሁኔታ እያሳየ ነው። ወያኔ ዛሬም የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲውን አጠንክሮ የቀጥለ ሲሆን፤ በተለይ ባሁኑ ወቅት በሙስሊምና በክርስቲያን ኢትዮጵያውያን መካከል ቅራኔና ግጭት ለመፍጠር በቀጥታም ሆነ በተዛዋሪ እየፈጸመ ያለው ወንጀል ሀገሪቱን እጅግ የሚያሰጋና ወገንን ሁሉ የሚያሳስብ አንገብጋቢ ጉዳይ ሆንዋል።

የፖለቲካውን ሂደት ስናይም ደግሞ ሁኔታው ይበልጥ አደገኛና አስፈሪ እንጂ የተሻለ አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ የጭቆና አገዛዝ በቃኝ ብሎ ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ ቆርጦ የተነሳ ስለመሆኑ በግንቦት1997 ያረጋገጠው ወያኔ፤ ከዚያ ታሪካዊ ወቅት ጀምሮ፤ የመሸንገያ-ዴሞክራሲ ጭምብሉን አውልቆ በመጣል ሥርአቱ የአንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ መሆኑን በገሐድ እያሳዬ በመምጣት ዛሬ ከጡዘቱ ላይ አድርሶታል። ፖሊስ፤ የጦር ሃይሉ፤ የድህንነት ጥበቃ መሥሪያ ቤትና ፍርድ ቤቶች ሙሉ የአገዛዙ ጥቅም ማስጠበቂያዎችና መገልግያዎች ሆንዋል። ሕግም በሀገሪቱ ቦታ ተንፍጓል። ሰላምዊ አላማዎች ይዘው የሚንቀሳቀሱ የፖለትካ ፓርቲዎችና የሲቪክ ማኅበራት እንዲሁም ነፃው ፕሬስ የአገዛዙ የጥቃት ኢላማዎችና ሰለባዎች ተደርገዋል።

ከሁሉም በላይ ወያኔው በአሁኑ ወቅት የአንድነት ለዴሞክርሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀ መንበር ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳንና ሌሎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ የቆሙ ታጋዮችን በማሰር የወሰደው እርምጃ፤ ሙሉ በሙሉ ተስፋ መቁረጡንና አጥፍቶ ለመጥፋት እየተወራጨ መሆኑን አረጋግጧል።

በዚህ አኳያ እዚህ ምእራብ አውስትራሊያ የምንኖር ኢትዮጵያውያን ከሰሞኑ በ“ግንቦት ’97 መንፈስ አንቀሳቃሽ ቡድን” አስተባባሪነት አስቸኳይ ስብሰባ አካሂደን በወቅቱ የአገራችን ሁኔታ ላይ ከተወያየን በኋላ የሚከተለውን መግለጫና ውሳኔ አስተላልፈናል።

1ኛ. የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ መታሰር እጅግ ያሳዘነንና ያንገበገበን መሆኑን እየገለጽን
በአስቸኳይ እንድትፈታ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ የምንኖር ኢትዮጵያውያን ሁሉ ተግተን
እንድንታገል ጥሪ እናቀርባለን።

2ኛ. እንደነ አቶ አበራ የማነ ዓብና አቶ ፀጋዬ ገብረመድኅን አርአያ ለረጅም ጊዜ የተንገላቱና
እንደ ቴዎድሮስ ካሳሁን በግፍ የታሰሩ እንዲሁም ሌሎች በሺዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካና
የሕሊና እስረኞች በአስቸኳይ እንዲፈቱ በጋራ የተጠናከረ ትግል እንዲናደግ ለመላው
የ|ትዮጵያ ሕዝብ ጥሪ እናቀርባለን።

3ኛ. በአንድ የፖለቲካ ፓርቲና ደጋፊዎቹ ላይ የወያኔ ኢህአዴግ መንግስት የሚፈጽመው ዋከባና
አፈና ለማንም የሚጠቅም ባለምሆኑ፤ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች እርስ በርስ ከመሻኮት ይልቅ
የአገርንና የወገንን ብሶት በማስቀደም በአንድነት ሥርአቱን ታግለው በምትኩ ፍትሐዊና
ዴሞክራሲያዊ ሕዝባዊ መንግስት የመመሥረት ሃላፊነት እንዲሰማቸውና ይህንንም በተግባር
እንዲወጡ ጥሪ እናደርጋለን።

4ኛ. የወያኔ መንግስት የጭካኔ አገዛዙን እድሜ ለማራዘም ወገናችንን በጎሣ ቅራኔ ለማፋጀት
የቻለውን ሁሉ አድርጎ ሲከሽፍበት፤ የሃይማኖት ግጭት ለመጫር የደመ ነፍስ ሩጫ እያደረገ
ስለሆነ ሕዝቡ በኢትዮጵያዊ ጨዋነት አንድነቱን ጠብቆ እንደገና እኩዩን እቅድ እንዲያከሽፍ
በጥልቅ ወገናዊ ስሜት እያሳሰብን፤ ከዚሁ ጋርም ሕዝቡ ወያኔ የኢትዮጵያን መሬት አሳልፎ
ለመስጠት የሚያደርገውን ሩጫ በጋራ እንዲታገል እንጠይቃልን።

5ኛ. ሕዝቡ በድርቅ፤ በሥርአቱ ብልሹነትና ንቅዘት እንዲሁም በዓለም ቀውስ ምክንያት
እየደረሰበት ያለውን ችግር በዝምታ መቀበል ሳይሆን ዘራፊው ገዢ ቡድን የነጠቀውን ሀብት
ለማስመለስ የሚችልበትና የኤኮኖሚ ነፃነት የሚያገኝበት የጋራ ጥረት እንዲያደርግና
እንዲረዳዳ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኖራለች!!
ሕዝባዊ ትግሉ ያሸንፋል!!

በምእራብ አውስትራሊያ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን
የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም
ፐርዝ

www.ethiomedia.com